# የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስታንዳርድ

(የተሻሻለ)

ታህሳስ 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ትም/ቢሮ

**ርዕስ**

**ገጽ**

1 መግቢያ ....3
2 ዓላማ ....3
3 የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ሥርዓት መዋቅር ....4
3.1 የመጀመሪያ ሳይክል /9-10/....4
3.2 የሁለተኛ ሳይክል /11-12/ ....4
4 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አደረጃጀት....5
4.1 የቦታ አመራረጥ መመዘኛዎች....5
4.2 የምድረ ግቢው ገፅታ አደረጃጀት....6
4.3 የምድረ ግቢው ስፋት....6
4.4 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ህንፃ አደረጃጀት /9-12/ ....7
4.4.1 የመማሪያ ክፍሎች ስፋት በሜትር ካሬ ....7
4.4.2 የአስተዳደር ህንፃ /ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ ....8
4.4.3 የተማሪዎች መፀዳጃ ....8
4.4.4 የቤት መፅሐፍት ህንፃ /ብሎክ/....9
4.4.5 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቤተ ሙከራ ክፍል /ህንፃ ....10
4.4.5.1 የፊዚክስ፣ ላቦራቶሪ ክፍል /ብሎክ/ስፋት በሜትር ካሬ ....10
4.4.5.2 የኬሚስትሪ ላቦራቶሪ ክፍል /ብሎክ/ ....10
4.4.5.3 የባዬሎጂ ላቦራቶሪ ክፍል/ብሎክ/ስፋት በሜትር ካሬ ....10
4.4.5.4 የሂሣብ ክፍል ብሎክ ስፋት በካሬ ሜትር ....10
4.4.5.5 ከሳይንስ ውጪ ለሚሰጡ ትምህርቶች የሚገለግሉ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት ክፍሎች ....11
4.4.6 የመሰብሰቢያ አዳራሽ /ብሎክ/....11
4.4.7 የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ....11
4.5 ለተለያዩ ክፍሎች አስፈላጊ የሆኑ ፈርኒቸሮችና ቁሳቁሶች ....12
4.5.1 የመማሪያ ክፍል ....12
4.5.2 የላቦራቶሪ ክፍል ....12
4.5.3 የሂሳብ ትምህርት ክፍል....13
4.5.4 የቢሮ ፈርኒቸሮችና ቁሳቁሶች....13
4.5.5 ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚያስፈልጉ የሰውነት ማጎልመሻና ስፖርት ትምህርት ቁሳቁስ....14
4.5.6 ለመማር ማስተማር ሂደት ድጋፍ ሰጪ የሆኑ ልዩ ልዩ አገልግሎት መስጪያ ክፍሎች የሚስፈልጉ ቁሳቁሶች 18

4.5.6.1 ቤተ መፅሐፍት ........18
4.5.7 ICT ማዕከል ........21
4.5.8 ትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ........21
4.5.8.1 የቢሮ ዕቃዎችና መሳሪዎች ........21
4.5.8.2 የእጅ መሳሪያዎች ........22
4.5.9 የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ........23
4.5.10 የመምህራንና ተማሪዎች መዝናኛ ክበብ ........24
4.5.10.1 የመምህራንና የሠራተኛና ክበብ ........24
4.5.10.2 የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ ........24
4.5.11 የአዳራሽ አጠቃቀም ........25
4.6 ለየትምህርቱ ዓይነቱ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች ........25
4.6.1 ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ........26
4.7 የተማሪ መፅሐፍት ጥምርታ ........27
4.8 የተማሪ ክፍል ጥምርታ ........27
4.9 የሰው ኃይል ምደባ ........27
4.9.1 የመምህራንና የሠራተኞች ተፈላጊ የትም/ደረጃ ........27
4.9.2 የልዩ ትምህርት መምህራንና የሠራተናች ድልድል ........29
5 የማስተማሪያ ዘዴ ........30
6 የሁለተኛ ደረጃ መምህር ፕሮፋይል ........30
6.1 ከሁለተኛ ደረጃ መምህራን የሚጠበቁ ባህሪይ ........31
7 የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ፕሮፋይል ........32
8 የማስተማር መማር ሂደት መመሪያዎች ........32
8.1 የትምህርት አመራርና አስተዳደር መመሪያዎች ........33
9 የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት ........34
9.1 የትምህርት ዓይነቶች የክፍለ ጊዜ ስርጭት ........35
9.1.1 በመጀመሪያ ሳይክል /9-10/ የሚሰጡ የትም/ዓይነቶችና የክፍለ ጊዜ ብዛት ........35
9.1.2 በሁለተኛ ሳይክል /11-12 /የሚሰጡ የትም/ዓይነቶችና የክፍለ ጊዜ ብዛት ........36
10 የትምህርት ወቅት ........38
10.1የት/ቤት ሰዓት ........38
10.2 የተጓዳኝ ትምህርት ........39
11 የመረጃ አያያዝና ፍሰት ........40
12 የትምህርት ደረጃ ምዘናና ማጠናቀቂያ መረጃ ........41
13 በማረጋገጫ የውስጥ የትም/ማስረጃዎች ........42
14 የት/ቤት ፣የአካባቢ ማህበረሰብ /ኮሙኒቲ/ እና የወላጅ ግንኙነት ........42

## 1. መግቢያ

የአንድ አገር ሥልጣኔና ዕድገት ሊገነባ የሚችለው አገሪቱ ባላት የተማረ የሰው ሀይል መሰረት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የመልካም አስተዳደርና ፈጣን የልማት ስትራቴጂን ተግባራዊ የሚያደርግ፣ የህዝብና የሀገር ችግሮችን ለመፍታት የተዘጋጀና ሀላፊነት የሚሰማው ከተፈጥሮ ተጽዕኖ በተግባር ለመላቀቅ የተዘጋጀ የማምረትና የመመራመር አቅሙ የዳበረ ዜጋ ለማዘጋጀት የሚያስችል የአጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ተቀርጿል፡፡ የትምህርት ፖሊሰውን መሰረት በማድረግ በአገሪቱ ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የትምህርት እንቅስቃሴ እንዴት መካሄድ እንዳለበት፣ ምን ምን ዓላማዎች ሊኖሩት እንደሚገባ በትምህርት ፖሊሲው ተካተዋል…

ይኸ የተቀረፀው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ውጤታማ እንዲሆን ደግሞ የትምህርቱ እንቅስቃሴ ጥራት በየወቅቱ መለካት መቻል አለበት፡፡ ለዚሁም የኢትዩጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የትምህርት ሚኒስቴር ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ በ1987ዓ.ም. የትምህርት ስታንዳርድ ለየትምህርት እርከኑ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረጉ የሚታወስ ነው፡፡ በዚህ ስታንዳርድ አማካኝት ትምህርት ሚኒስቴር በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የትምህርት እንቅስቃሴ ጥራት ለማስጠበቅ አስፈላጊ ጥረት አድርጓል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ይኸንን የትምህርት ስታንዳርድ አገሪቱ ካለችበትና ከደረሰችበት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታዎች አንፃር ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ ይኸ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስታንዳርድ የአዲስ አበባ ከተማን ተጨባጭ ሁኔታን መሠረት በማድረግ ተሻሽሎ ቀርቧል፡፡

## 2 ዓላማ

ይኸ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስታንዳርድ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- በተማሪው ላይ ለማምጣት የተፈለገውን ባህርይ በግልፅ ለማስቀመጥና ለመለካት እንዲቻል፣
- በትምህርት ቤተ ለመማር ማስተማር ሂደት መሳካቱ መሟላት የሚገባቸው ቁሳቁሶችንና ፋሲሊቲዎችን ለመወሰን፣

- የትምህርት ቤቱና የአካባቢ ህብረተሰብ ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር፣
- በትምህርት ቤቱ ሊኖር የሚገባውን የሰው ኃይል ለመወሰን፣
- የትምህርት ቤቱ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ከትምህርቱ አንቅስቃሴ አመቺነት አንፃር ምን መምሰል እንደሚገባቸው በግልፅ ለማስቀመጥ ነው፡፡

## 3 የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ሥርዓት መዋቅር

በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሰረት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት ሳይክል ተከፍሎ የሚሰጥ ሲሆን በመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ከ9ኛ– 10ኛ ክፍል በሁለተኛ ሳይክል ደግሞ ከ11ኛ–12ኛ ክፍል የሚሰጥ ነው፡፡

3.1 **በ2ኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል እድሜያቸው 15 ዓመትና ከዚያም በላይ ለሆናቸው ተማሪዎች የአጠቃላይ ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን በሚከተሉትን ነጥቦች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡**

- በዚህ እርከን የሚሰጥ ትምህርት ተማሪዉ በአግባቡ ትምህርቱን እንዲረዳው፣ ያለውን የግል ተስጥኦውን ተረድቶ የወደፊቱን ፍላጎቱን እንዲገነዘብና ለቀጣዩ ትምህርት የሚስማማውን የትምህርት መስክ እንዲመርጥ የሚያዘጋጀው ነው ::
- በዚህ ሳይክል የሚሰጠው የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ነው፡፡

3.2 በ2ኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት እድሜያቸው 17 ዓመትና ከዚያም በላይ ለሆኑ ተማሪዎች ከአጠቃላይ ትምህርት ጋር ተዛምዶ የሚሰጥና ተማሪዎች በቂ ችሎታና ክህሎቶች ገብይተው እንዲጨርሱና ለከፍተኛ ትምህርት በብቃት እንዲዘጋጁ የሚያደርግ ነው::

የልዩ ፍላጎት ትምህርትም የመደበኛውን ትምህርት መዋቅር የሚከተል ነው፡፡ ነገር ግን በአካልና በአእምሮ ችሎታ ችግር ምክንያት ለመደበኛ ትምህርት ታስቦ የወጣውን እርከን ከሌሎች ተማሪዎች በእኩል መዝለቅ አይችሉም፡፡ በሌላ በኩል በጣም የመጠቀ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ደግሞ የተለየ ችሎታ በሚያሳዩበት ትምህርት ዓይነት እንዲገፉበት ሁኔታዎች ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ ሁለት የተለያዩ ባህሪያት ያላቸው ወጣቶች ችሎታ ያለው መምህር ተመድቦ ተጨማሪ እገዛ እንዲያደርግላቸው ይደረጋል። ስለሆነም በተለያዩ ዘርፎች ላይ የሚገኙት ልዩ ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በአብዛኛው በሚከተሉት የትምህርት እርከኖች ሊሳተፉ ይችላሉ።

| | የልዩ ፍላጐት ትምህርት ወጣቶች | የትምህርት እርከን | |
|---|---|---|---|
| | | 9–10 | 11–12 |
| 1 | ማየት የተሳናቸው | ይሳተፋሉ | ይሳተፋሉ |
| 2 | መስማት የተሳናቸው | ይሳተፋሉ | ይሳተፋሉ |
| 3 | የስሜት መረበሽ ያለባቸው | እንደሁኔታው | እንደሁኔታው |
| 4 | መናገር የተሳናቸው | ይሳተፋሉ | ይሳተፋሉ |
| 5 | የአካል ጉዳት ያለባቸው | ይሳተፋሉ | ይሳተፋሉ |
| 6 | ተደራራቢ ጉዳት ያለባቸው | እንደ ሁኔታው | እንደሁኔታው |
| 7 | የጎዳና ላይ ተዳዳሪ | ይሳተፋሉ | ይሳተፋሉ |
| 8 | ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው | ይሳተፋሉ | ይሳተፋሉ |

## 4. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አደረጃጀት

### 4.1 የቦታ አመራረጥ መመዘኛዎች

ጥራት ያለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለማስፋፋት ት/ቤቶቹ ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር አንድ ት/ቤት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

- ተማሪዎች ተመላልሰው ሊማሩ የሚችሉበት ሆኖ ከተማሪዎች መኖሪያ ክልል አማካይ ርቀት ከ3–5 ኪሎ ሜትር ያልበለጠ /እንደየ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል/
- የመኪና መንገድ፣ መገናኛ ያለው ወይንም ከመገናኛ መንገድ ቅርበት ያለው
- የአካባቢውን ጸጥታ ከሚያውኩ ከትራፊክ መጨናነቅ፣ ከመጠጥ ቤቶች፣ ከገበያ ፣ከወንዝ፣ ከጫት መቃሚያ ቤቶች፣ ከሙዚቃ ቤቶች የራቀ፣

- የት/ቤቱ ግቢ ወጣ ገባ ያልበዛበት ወይም ሜዳማ የሆነ ቦታ ያለው፣
- ለትምህርት ኘሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆን በቂና ተስማሚ የእስፖርትና የጓሮ አትክልት ቦታ ያለው ፤
- የመሬቱ አቀማመጥ ለጎርፍ ፤ ለፍሳሽ ለከባድ ንፋስና ለአቧራ ያልተጋለጠ፤
- የውኃ የመብራትና ስልክ አገልግሎት ያለው፤

4.2 የምድረ ግቢው ገጽታ አደረጃጀት

የሚቋቋሙ ት/ቤቶች በተማሪዎች የመማርና የማስተማር ውጤቶች ላይ ተፅዕኖ ከሚያስከተሉ ነገሮች ነፃ መሆን አለባቸው፡፡ አንድ ት/ቤት የሚከተሉት ገጽታና አደረጃጀት ይኖሩታል፡፡

- ለመማሪያና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ብሎኮችና ክፍሎች እንደ ሥራ ቅርበታቸውና አገልግሎታቸው የተሰሩ፤
- የህንፃዎች አደረጃጀት የምድረ ግቢውን ውበት አጠባበቅ ግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ የመኪና ማቆሚያና የእግር መንገዶች እንደ አስፈላጊነቱ የተሠራለት ፣
- የመዝናኛ መጫዎቻ ቦታዎች / ሜዳዎች/ ያሉት
- በአጥር የተከለለና የተከበረ፤
- ከክፍል ውጭ ለሚሰጡ ትምህርቶች /የጓሮ አትክልት፣ጤሰማ፣ወዘተ.../ ተመጣጣኝ ቦታ በግቢው ውስጥ ያሉት ፣
- በአጠቃላይ የህንፃዎች አደረጃጀትና የመንገዶች አቀማመጥ ለትምህርት አሰጣጥ አመቺና መስኀብ ያለው ይሆናሉ፡፡

4.3 የምድረ ግቢው ስፋት

አንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሊኖረው የሚገባው የምድረ ግቢው ስፋትና መጠን እንደተማሪዎች የዕድገት ደረጃና የእንቅስቃሴ ሁኔታ የተለያዩ ትምህርት ኘሮግራሞች ሊያቅፍ ስለሚችል መነሻ 6000-30000 ሜትር ካሬ ስፋት ያለው ቦታ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም በከተማና በገጠር እንደየሁኔታው ሊለያይ የሚችል ሲሆን በገጠር የትምህርት ቤቶችን የውስጥ ገቢ ለማጠናከር እንዲቻል የተቀመጠው አሐዝ ባለበት የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ነገር ግን በከተማ የለውን የቦታ ጥበት ለመቅረፍ የት/ቤቶች ህንፃዎች ፎቆች ሊሆኑ እንደሚችሉ እና እንዲሁም የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ሶስት በአንደ (ሁለገብ የስፖርት ሜዳ

ባለ64×75=4800 ካ.ሜ እንዲሁም ትንሹ ሜዳ 10×20=200ካ.ሜ /ከአንድ የእስፖርት ዓይነት/ በላይ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገው) ይዘጋጃሉ።

### 4.4 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሕንፃ አደረጃጀት (ከ9–12 ክፍል)

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሕንፃ እንደየባህሪያቸው ተለያይተው የተሰሩና ለጤናማ የመማር ማስተማር ሂደት በዕቅድ፣ በአቅምና ለብዙ አካባቢዎች በማዕከልነት ተሰባስበው የሚገለገሉበት ስለሚሆን ከብሎኬት ከሸክላ ወይም ከድንጋይ እንደ አካባቢው የአየር ንብረትና የማቴሪያል አቅርቦት እየታየ ሊሰራ ይችላል።
- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ህንጻዎች ልዩ ፍላጎት ላላቸውና ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆን አለባቸዉ፡፡
- የሕንፃው አደረጃጀትም በተመለከተ አንድ ወጥ በመሆኑ ከ9–12 ወይም በተናጠል ከ9–10 እና ከ11–12 ተብሎ እንደየእድገት ደረጃው ሊዋቀር ይችላል።

**የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (9-12) የህንጻዎች አደረጃጀት እንደየፕሮግራሙ ሁኔታ ተፈላጊ የሆኑ የሚከተሉት ህንፃዎች ይኖሩታል፡፡**

#### 4.4.1. የመማሪያ ክፍሎች ስፋት በሜትር ካሬ

- አንድ የመማሪያ ክፍል ቢያንስ ለ10 ተማሪዎች የሚበቃ ሆኖ መጠኑ ከ35 እስከ 46.08 ( 7.20×6.40 )ካ.ሜ ይሆናል፡፡/የአንድ ተማሪ ይዞታ በ1.15ሜትር ካሬ ስሌት/ በዚሁ መሠረት የባለ አራት የመማሪያ ክፍል የብሎኩ መጠን ከ140-211.58 ይሆናል፡፡
- የመማሪያ ክፍሎችና ብሎኮች ትምህርት ቤቱ በሚኖረው የተማሪ ብዛት እና በአካባቢው የአየር ፀባይ መሰረት የሚወሰን ሲሆን የትምህርቱን ሥራ በአግባቡ ለመምራትና ውጤታማ የማስተማርና መማር ሂደት ለማካሄድ እንዲቻል የቤቱ ቁመትና የመስኮቶቹ ስፋት ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት። አንድ ትምህርት ቤት ከ3000 ተማሪዎች በላይ ማስተናገድ

4.4.2 **የአስተዳደር ሕንፃ /ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ**

| ተ.ቁ | ክፍል/ቢሮ | መጠን/ስፋት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | የርዕሰ መምህር ቢሮ | 4×5=20 | |
| 2 | ም/ ርዕሰ መምህርት ቢሮ | 4×5=20 | |
| 3 | የአስተዳደር ቢሮ | 3.55×3.53=12.53 | |
| 4 | የመዘክር ክፍ□ . | 3.55×3.53 =12.53 | |
| 5 | የፀ□ፊ ቢ□ | 3.00×3.53=10.59 | |
| 6 | የመምህራን ማረፊያ | 3.70×7.60=28.12 | |
| 7 | የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ክፍል | 3.×4.=12 | |
| 8 | ንብረት ክፍል | 5.55×6.70=37.19 | |
| 9 | ጽዳት ሠራተኛ ክፍል | 3×2=6 | |
| 10 | መጸዳጃ ቤት ለመምህራ ለአስተዳደር ሰራተኞች | 2×4=8 | ጾታን ታሳቢ ያደረገ አንድ ክፍል 2 ካሜ |
| 11 | 2 የጥበቃ ቤት (እንደየ ት/ቤቱ ሁኔታ ይወሰናል) | 2×3=6 | |
| 12 | የሚይንዲስሪቢዩሽን / የኤሌክትሪክ ዋና ማከፋፈያ / ያለበት ክፍል | 1.00×1.48=1.48 | |
| | | | |

4.4.3 **የተማሪዎች.መጸዳጃ**

**የወንድና የሴት መፀዳጃ ቤቶች በተለያየ ቦታ ፊትና ጀርባ ሆነው የሚሠሩ ሲሆን፣**

4.4.3.1 **የወንዶች ደረቅ መዳጃ ቤት / ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ**

- ባለ 8 ቀዳዳ ደረቅ ሽንት ቤት የአንዱ ሽንት ቤት መጠን 4×4 =16 ሲሆን በጥቅሉ 1 ቀደዳ ለ20 ተማሪ ሂሳብ መሆን አለበት፡፡
- የእጅ መታጠቢያ ቧንቧ ይኖረዋል፡፡

4.4.3.2 የሴቶች ደረቅ መጸዳጃ ቤት / ብሎክ/

- ከላይ በተራ ቁጥር 4.4.3.1 እንደተጠቀሰው መጠኑ እኩል ነው
- የእጅ መታጠቢያ ቧንቧ ይኖረዋል።

4.4.4 የቤተ መጻሕፍት ሕንፃ / ብሎክ/

➢ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቤተመፃህፍት ህንፃ ስፋት የሚወሰነው በዓመቱ ውስጥ ከሚመዘገቡት የተማሪዎች ቁጥር ከ5-10 በመቶ በአንድ ጊዜ ሊያስተናግድ በሚችል ሆኖ።

መጻሕፍት በሚመደቡበት ወቅት 10 በመቶ ልብወለድና 90 በመቶ ደግሞ ማጣቀሻ መጻሕፍት ይመደባሉ።

በአጠቃላይ ለሁሉም ት/ቤቶች ለአንድ ተማሪ በአማካኝ ከ4 እስከ 5 መፃህፍት እንዲደርሳቸው ታስቦ ቤተ መፅሐፍቱ መደራጀት አለበት።

በሁለተኛ ደረጃ የሚቋቋም ቤተመጻሕፍት የሚከተሉትን የሥራ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

➢ የተማሪዎች የማንበቢያ ክፍል 10 ሜትር x 10 ሜትር = 100 ካሬ ሜትር፣

➢ ስፋቱ 5ሜ x 5ሜ =25 ካሬ ሜ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ መጻፍህት ስራ ማከናወኛ ክፍል

➢ የመጻሕፍት ማዋሻና መቀበያ ስፍራ5×4=20 ካሬ ሜትር፣

➢ የአዳዲስ መጻሕፍትና መፅሔቶች ማስተዋወቂያ ስፍራ9 ካሬ ሜትር

➢ የመምህራና ሠራተኛ ማንበቢያ ክፍል 20 ካሬ ሜትር ይኖሩታል፣

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቤተመጻሕፍት ህንፃ ፣ የሠራተኞች ክፍሎችን፣ ማንበቢያ፣ መጻሕፍት ማስቀመጫ ክፍሉች እንዲሁም የት/ቤቱ ተማሪዎች በአግባቡ ማስተናገድ የሚችል ሆኖ መደራጀት አለበት።

| የተማሪዎች | የቤተመፃህፍት ሠራተኞች ብዛት | የቤተመፃህፍቱ ማንበቢያ ክፍል | ቤተመፃህፍቱ ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ የመጻሕፍት ብዛት |
|---|---|---|---|

| ብዛት | የሠለጠነ ባለሙያ | ረዳት ሠራተኛ | የወለሉ ስፋት በአንድ አካባቢ | በአነስተኛ ግምት መቀመጫዎች | የንባብ ክፍሎች | ዓይነት | ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 200-400 | 1 | 1 | 1ካሜ | 50 | 1 | 500 | 1,000 |
| 401-500 | 1 | 1 | 1ካሜ | 60 | 1 | 1,200 | 2,500 |
| 501-1200 | 1 | 1 | 1ካሜ | 75 | 1 | 2,500 | 5,000 |
| 1201-2500 | 1 | 1 | 1ካሜ | 100 | 1 | 5,000 | 10,000 |
| 2501-3000 | 2 | 1 | 1ካሜ | 100 | 2 | 7,500 | 15,000 |
| 3000 በላይ | 3 | 2 | 1ካሜ | 100 | 2 | 10,000 | 20,000 |

### 4.4.5. የሁለተኛ ደረጃ ት/□ት ቤተ ሙከራ ክፍል /ህንፃ/

ለፊዚክስ፣ ለኬሚስትሪና ለባዮሎጂ የሳይንስ ትምህርቶች ልዩ ልዩ ኬሚካሎች፣ አፓራተስና ኢኩፕመንት የሚያገለግሉ ዕቃዎች የሚቀመጡበት ስቶርና መምህሩ ትምህርቱን ከማቅረቡ በፊት ልምምድ የሚያደርግበት የዝግጅት ክፍል እንዲሁም ተማሪዎች የሚለማመዱበት የዲሞኔስትሬሽን ክፍል ያስፈልጋል፡፡

#### 4.4.5.1 የፊዚክስ ላብራቶሪ ክፍል/ ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ

| ተ.ቁ | ክፍል | መጠን | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዴሞንስትሬሽን ክፍል | 15.9×5.85=92.92 | |
| 2 | ዝግጅት ክፍል ና ስቶር | 2.40×5.80=13.92 | |
| 4 | በአጠቃላይ የብሎኩ መጠን | 24.44×6.25=152.75 | |

#### 4.4.5.2 የኬሚስትሪ ላብራቶሪ ክፍል/ ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ

| ተ.ቁ | ክፍል | መጠን | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዴሞንስትሬሽን ክፍል | 17.70×5.85=92.92 | |
| 2 | ዝግጅት ክፍል | 2.40×5.80=13.92 | |
| 3 | ስቶር | 3.30×5.80=19.14 | |
| 4 | በአጠቃላይ የብሎኩ መጠን | 24.44×6.25=152.75 | |

4.4.5.3 **የባዮሎጅ ላባራቶሪ ክፍል** ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ

| ተ.ቁ | ክፍል | መጠን በሜትር | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዴሞንስትሬሽን ክፍል | 15.×5.55=78.975 | |
| 2 | ዝግጅት ክፍል | 2.4×2.86=6.86 | |
| 3 | ስቶር | 3.3.30×2.85=9.4 | |
| | አጠቃላይ የብሎክ መጠን | 6×18=108 | |

4.4.5.4 **የሂሳብ ክፍል** ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ

| | ሂሳብ ክፍል | | |
|---|---|---|---|
| 1 | ክፍል | 6.92×7.26=50.24 | |

4.4.5.5 **ከሳይንስ ውጪ ለሚሰጡ ትምህርቶች የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት ክፍሎች**

ከሳይንስ ውጪ ለሆኑ የሶሻል ሳይንስ ትምህርቶች እንደ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ ኢኮኖሚክስ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣የቴክኒካል ድሮዊንግም ትኩረት ስለሚሰጣቸው ለእነዚህ ትምህርቶች የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት የየራሳቸው ክፍል እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

| ተ ቁ | ክፍል | መጠን በሜትር | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | አይሲቲ | 8×7= 56 | ከ9ኛ - 12ኛ |
| 2 | የሳትላይት | 4×4=16 | ከ9ኛ - 12ኛ |
| 3 | አይቲ | 8×7 =56 | ለመሰናዶ ብቻ |
| 4 | የቴክኒካል ድሮዊንግ | 8x7=56 | ለመሰናዶ ብቻ |

ማሳሰቢያ፣

1/ ከላይ ከ1 እስከ 4 የተጠቀሱት ክፍሎች ብዛት እንደ ተማሪዎች ብዛት ይወሰናል።

2/ በአይሲቲ ክፍል ውስጥ መኖር የሚገባው የኮምፒውተር ብዛት እንደ ተማሪው ብዛት የሚወሰን ይሆናል።

4.4.6 **የመሰብሰቢያ አዳራሽ /ብሎክ/**

**አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለመምህራንና ለተማሪዎች መሰብሰቢያ የሚያገለግል መጠኑ 200 ካሬ ሜትር ስፋት የሆነ አዳራሽ ሊኖረው ይገባል፡፡ አዳራሹ የተሟላ ፋሲሊቲ ይኖረዋል።**

4.4.7 **የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል**

**አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ችሎታቸውንና ዝንባሌያቸውን የሚፈትሹበት አንድ ወርክሾፕ 10ሜ × 8 ሜ =80 ሜ .ካ እና ስቶር 10 ሜ X 7 ሜ= 70 ካ ሜ ያለው የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ሊኖረው ይገባል፡፡**

## 4.5 **ለተለያዩ ክፍሎች አስፈላጊ የሆኑ ፈርኒቸሮችና ቁሳቁሶች**

**የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመማሪያ ክፍሎች፣ቤተሙከራ፣ቤተመጽሀፍት፣ቢሮዎች፣ የሂሳብ ትምህርት ክፍል ፣የትምህርት ማበልጸጊያ፣ የአይሲቲ ማዕከሎች፣ የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ፣ የሰውነት ማጎልመሻ፣ ደረጃቸውን በጠበቁ ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡**

### 4.5.1 **የመማሪያ ክፍል**

| ተ.ቁ | መጠን በሴንቲ ሜትር | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የመማሪያው ዓይነት | ብዛት | ርዝመት | ወርድ | ቁመት | ምርመራ |
| 1 | /ወንበርና ጠረጴዛ/ | 20 | 55 | 100 | 74 | በ1 ዴስክ 2 ተማሪዎች የሚያስቀምጥ |
| 2 | ጠረጴዛ | 1 | 80 | 120 | 74 | የመምህሩ |
| 3 | ወንበር | 1 | 40 | 56 | 78 | የመምህሩ |
| 4 | ዴስክ | 40 | 35 | 35 | 77 | የተማሪው |
| 5. | የጠመኔ ሰሌዳ | – | 5 | 1.20 | | ለአንድ መማሪያ ክፍል |
| 6. | ማስታወቂያ ሰሌዳ | 1 | – | 1.2 | 2.20 | |

### 4.5.2 **የላብራቶሪ ክፍል**

| ተ.ቁ | የእቃው ዓይነት | ብዛት | | | መጠን በሴንቲ ሜ. | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ፊዚክስ | ባዮሎጂ | ኬሚስትሪ | ስፋት | ወርድ | ቁመት |
| 1 | በርጩማ ስቱል | 42 | 42 | 42 | 32 | – | 54 |
| 2 | የመምህሩ ወንበር | 1 | 1 | 1 | 40 | 56 | 78 |
| 3 | የመምህር ጠረጴዛ | 1 | 1 | 1 | 120 | 60 | 75 |
| 4 | የመምህሩ ዲሞንስትሬሽን ጠ | 1 | 1 | 1 | 80 | 220 | 85 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ረጴዛ | | | | | | |
| 5 | የተማሪዎች አግዳሚ ጠረጴዛ | 20 | 20 | 20 | 55 | 110 | 82 |
| | ቁምሳጥን፡<br>- ላይ<br>- ታች | <br>4<br>4 | <br>4<br>4 | <br>4<br>4 | <br>120<br>120 | <br>40<br>60 | <br>110.2<br>82.2 |
| 7 | ማሳያ ቁምሳጥን<br>- ላይ<br>- ታች | <br>1<br>1 | <br>1<br>1 | <br>1<br>1 | <br>120<br>120 | <br>40<br>50 | <br>67.7<br>82.6 |

### 4.5.3 የሂሳብ ትምህርት ክፍል ፈርኒቸርና ቁሳቁሶች

| ተ.ቁ. | የዕቃው ዓይነት | መጠን በሴንቲ ሜትር | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | ርዝመት | ወርድ | ቁመት |
| 1 | ካፕ ቦርድ | 1 | 120 | 50 | 200.4 |
| 2 | ጠመኔ ሰሌዳ | 1 | 240 | – | 120 |
| 3 | የግራፍ ሰሌዳ | 1 | 120 | – | 120 |
| 4 | ማስታወቂያ ሰሌዳ | 1 | 120 | – | 120 |
| 5 | የመምህሩ ወንበር | 1 | 40 | 56 | 78 |
| 6 | የመምህሩ ጠረጴ□ | 1 | 60 | 120 | 75 |
| 7 | የተማሪ ዴስክ | 20 | 110 | 55 | 75 |
| 8 | የተማሪ ወንበር | 40 | 40 | 56 | 78 |
| 9 | ፋይሊንግ ካቢኔት | 1 | 45 | 60 | 130 |

### 4.5.4 የቢሮ ፈርኒቸርችና ቁሳቁሶች

| ተ.ቁ | ዓይነት | መጠን | | | ርዕሰ መም ቢሮ | መም ህራን | አስተ. ክፍል | ዕቃ ቤት ግምጃ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ስፋት | ወርድ | ቁመት | | | | | |
| 1 | ባለ መደገፊያ ወንበር | 40 | 56 | 78 | 1 | - | 1 | 1 | |

| ተ.ቁ | ዓይነት | መጠን | | | ርዕስ መምቢሮ | መምህራን | አስተ. ክፍል | ዕቃ ቤት ግምጃ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ስፋት | ወርድ | ቁመት | | | | | |
| 2 | ወንበር(መደገፊያ የሌለው) | 40 | 56 | 78 | 4 | 5-20 | 6 | 3 | |
| 3 | የቢሮ ዴስክ ባለ ኪስ | 80 | 160 | 74 | 1 | - | 2 | 1 | |
| 4 | የመሰብሰቢያ ጠረጴዛ | 80 | 150 | 74 | 1 | 2-6 | 1 | - | |
| 5 | ካኝቦርድ | 40 | 120 | 100 | 4 | - | 6 | 2 | ባለ 9 ተካፋች |
| 6 | ካኝቦርድ እንደ አስፈላጊነቱ | 40 | 120 | 200 | - | 2–6 | 2 | - | ባለ 9 ተካፋች |
| 7 | ፋይል ካብኔት | 45 | 62 | 135 | 1 | 2-6 | 1 | 1 | ባለ አራት ተካፋች |
| 8 | ታይፒስት ወንበር | 40 | 40 | 77 | 1 | - | 1 | 1 | |
| 9 | ታይፒስት ዴስክ | 50 | 75 | 65 | 1 | - | 1 | | |
| 10 | ሽልፍ | 120 | 40 | 200 | - | – | 2 | 8 | |
| 11 | ጠመኔ ሰሌዳ | 500 | 120 | – | - | 1 | - | | – |
| 12 | ማስታወቂያ ሰሌዳ | 120 | 120 | – | 2 | 1 | 1 | 1 | - |
| 13 | ቆሻሻ ማጠራቀሚያ | – | – | – | 1 | 1 | 1 | 1 | - |
| 14 | የፋይል ማቅረቢያ ትሪ | – | – | – | 2 | - | 2 | - | |
| 15 | ኮምፒውተር | – | – | – | 1 | – | 1 | 1 | |
| 16 | ፕሪንተር | – | – | – | 1 | | 1 | | |
| 17 | ፎቶ ኮፒ ማሽን | – | – | – | 1 | | | | |

4.5.5 **ለሁለተኛ ደረጃ ትም/የሚያስፈልጉ የሰውነት ማጎልመሻ ስፖርት ትምህርት ቁሳቁሶች**

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በቀለም ትምህርት ላይ የተመሰረተ ዕውቀት ብቻ ሳይሆን በአካልና በመንፈስ የዳበረ ዜጋ በማፍራት ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች በመደበኛ

ክፍለ ጊዜ የቀሰሙትን የንድፈ ሀሳብ ትምህርት በተግባር ለማሳየት የሚከተሉትን የትምህርት መሳሪያዎች ት/ቤቱ አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

| ተ ቁ | የመሣሪያ ዓይነት | የክፍል ደረጃ | መጠን/ ክብደት | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ኳሶች | | | | |
| 1.1 | እግር ኳስ | 9-12 | ቁጥር 5 | 5 | 1ለ80 **ተማሪዎች** |
| 1.2 | ቅርጫት ኳስ | 9-12 | ጁኒየር | 3 | |
| 1.3 | ቅርጫት ኳስ | 9-12 | ሲኒየር | 3 | |
| 1.4 | የእጅ ኳስ | 9-12 | መደበኛ ሲኒየር | 3 | |
| 1.5 | የመረብ ኳስ | 9-12 | መደበኛ ሲኒየር | 3 | |
| 2 | የአትሌቲክ መሣሪያዎች | | | | ለ80 ተማሪዎች |
| 2.1 | – ጦር | 9-12 | 600 ግራም | 2 | |
| 2.2 | – ጦር | 9-12 | 700 ግራም | 2 | |
| 2.3 | – ዲስከስ | 9-12 | 1.50 ኪ.ግ | 2 | |
| 2.4 | – ዲስከስ | 9-12 | 1.75 ኪ.ግ | 2 | |
| 2.5 | – አሎሎ | 9-12 | 5 ኪ.ግ | 2 | |
| 2.6 | -አሎሎ | 9–12 | 5.5 ኪ.ግ | 2 | |
| 2.7 | የከፍታ ዝላይ ቋሚ በጥንድ | 9–12 | ከብረት የተሰራ | 1 | በት/ቤት |
| 2.8 | የከፍታ ዝላይ አግዳሚ | 9–12 | | 1 | |
| 2.9 | የሩጫሰዓት መቆጣጠሪያ | 9–12 | ኤሌክትሮኒክስ | 1 | |
| 2.10 | – የሩጫ ማስነሻ ሳንቃ | 9–12 | | 1 | |
| 2.11 | – የሪሌይ ቅብብል ላዎች | 9–12 | 30ሣ ርዝመት | 8 | ከ50 ግራም ያላነሰ ክብድት ካለው እንጨት ወይም ስስ ቧንቧ የተሠራ |
| 3 | ጅምናስቲክ መሳሪያዎች | | | | |
| 3.1 | -ቢም | | | 1 | |

| ተ ቁ | የመሣሪያ ዓይነት | የክፍል ደረጃ | መጠን/ ክብደት | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3.2 | -ተደራራቢ ሳጥን | | | 1 | |
| 3.3 | -በክ | | | 1 | |
| 3.4 | – ፍራሽ | 9–12 | 1×3 ሜትር | 2 | |
| 3.5 | – ፍራሽ | 9–12 | 1×6 ሜትር | 2 | |
| 3.6 | -መንጠሪያ ሳጥን | | | 1 | |
| 3.7 | – የመዝለያ ገመድ | 9–12 | 1.50 ሣ ሜ ርዝመት | 20 | |
| 3.8 | – የመምህሩ ቱታ | 9–12 | የሀገር ውስጥ | 1 | በዓመት |
| 3.9 | የመምህሩ ታኬታ | 9–12 | | 2 | |
| 3.10 | – ፊሽካ | 9–12 | | 2 | |
| 3.11 | – የኳስ መንፊያ ጠምኘ | 9–12 | | 2 | |
| 3.12 | – የመረብ ኳስ መረብ | 9–12 | | 2 | የአገር ውስጥ |
| 3.13 | የባስኬት ቦል ቋሚ ከነሳንቃውና ከነቀለበቱ በጥንድ | 9–12 | | 1 | |
| 3.14 | መለኪያ ሜትር | 9–12 | ባለ 25 ሜትር | 1 | |
| 3.15 | መለኪያ ሜትር | 9–12 | ባለ 50 ሜትር | 1 | |
| 3.16 | የስፖርት ሹራብ /ማሊያ/ ከነቁምጣው | 9–12 | | 16 | |

### 4.5.6 ለመማር ማስተማር ሂደት ድጋፍ ሰጪ የሆኑ ልዩ ልዩ አገልግሎት መሰጫ ክፍሎች የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች

#### 4.5.6.1 ቤተ መጽሀፍት

- **በቤተመጽሃፍት የሚገኙ የማዳመጫና የእይታ /የመስሚያና የማያ/መሣሪያዎች፣**
    - በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚሰጠው ትምህርት በተግባር የተደገፈ እንዲሆን ቤተመጻሕፍቶቹ የሚከተሉትን የማዳመጫና የእይታ መሳሪያዎች አሟልተው መገኘት አለባቸው፡

| ዓይነት | መግለጫ |
|---|---|
| አትላስ | የካርታ መጻሕፈት |
| ሥዕሎች | ፎቶግራፎች ያጠቃልላል |
| ቻርቶች | ልዩ ልዩ አሃዛዊ መግለጫዎች የተመለከተ |
| ግሎፖች | ፊዚካል፤ ፖለቲካል . . . ወዘተ |
| ካርታዎች | በዓለም ፣በአህጉር፤ በሪጅ፤ በሀገር |
| ጥቅል የፎቶግራፍ ፊልሞች | ጂኦግራፊ፤ ሣይንስ ትም/ዓይነቶች ቋንቋ. . ወዘተ |
| ስላይድ የፎቶግራፍ ፊልሞች ባለ ድምጽና ድምጽ የሌላቸው ተንቀሳቃሽ ፊልሞች | የጂኦግራፊ ፤ ሣይንስ ትም/ዓይነቶች |
| ቴኘ ሪኮርድ | |
| የባህል መሣሪያዎች | የቴክኖሎጂ የአለባበስና ቅርሳ ቅርስ ስብስብ ያጠቃልላል |

**በአንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚቋቋም** ቤተ **መፅሐፍት የሚከተሉትን ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡**

- ወቅታዊ መጽሄፍት በተለያየ መንገድ በማሰባሰብ ለአከባቢውና ለት/ቤቱ ማህበረሰብ በማቅረብ የንባብ ፍላጐትን ማዳበር፤
- ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ መጻሕፍትን በጥራትና በዓይነት በማቅረብ የተማሪዎችና የመምህራንን ዕውቀት ማበልጸግ፣
- ማንኛውንም የጥናትና ምርመራ ሥራዎችን ለማካሄድ በምንጭነት ማገልገል፤
- የመጻሕፍትና የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም ዘዴዎችን ለማስተማር፤
- ትርፍ ጊዜን በንባብ ለማሳለፍ፡፡
- ለተማሪና ለመምህራን ተጨማሪ ዕውቀት የሚሰጡ መፅሐፍት (Supplementary books) በጥራትና በዓይነት ለማቅረብ፣
- ክግል ሀሳብ ይልቅ የጋራ አስተሳሰብን የሚያጐለብቱ ከጥላቻና ከአድሎአዊነት ይልቅ ትክክለኛ ምክንያቶችን የሚያስቀድሙ መፅሐፍት መርጦ በማቅረብ የህብረተሰብን ፍላጎትና አመለካከትን ማዳበር፣

- **በ2ኛ ደረጃ በት/ቤት ውስጥ የሚቋቋም ቤተመጻሕፍት የሚከተሉትን ነጥቦች ማካተት አለበት፡፡**
  - የሚቋቋመው ቤተመጽሀፍት በአንድ አማካይና ምቹ ቦታ ማደራጀት፣
  - ፀጥታና በቂ ብርሃን እንዲሁም ሰፊ የማንበቢያ ቦታ ያለው፣
  - የመጻሕፍት ብዛትና ዓይነቶችም እንደ ትምህርት ዓይነቶችና ተማሪዎች ቁጥር ከፍ ያለ መሆን
  - ቤተመጻሕፍት ተማሪዎችና መምህራን በሚያመቻቸው ሰዓት ማንበብ እንዲችሉ ክፍት እንዲሆን ማድረግ፣
  - ለዚሁም ሥራውን የሚመራ ተማሪውን ከቤተመጻሕፍት ሥርዓት ጋር የሚያስተዋውቅ በሙያው የሰለጠነና ለሥራው ተመጣጣኝ የሰው ኃይል መኖር አለበት፡፡
- **አንድ ስታንዳርዱን የጠበቀ የሁለተኛ ደረጃ ቤተመጽሕፍት የሚከተሉትን ዋና ዋና ፈርኒቸሮችና ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡**

| ተ.ቁ | ዓይነት | ብዛት | መጠን በሴንቲ.ሜ/ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መቀስ | 2 | | መካከለኛ |
| 2 | የቀን መቁጠሪያ ማኅተም | 1 | | |
| 3 | የቤተ መፃሕፍት ማኅተም | 1 | | |
| 4 | ስቴፕለር | 2 | | |
| 5 | የማኅተም መርገጫ | 1 | | |
| 6 | ዴት ዱዩ ካርድ | - | | |
| 7 | ማዋሻ ካርድ /መዝገብ/ | - | | |
| 8 | መቆጣጠሪያ ካርድ | - | | |
| 9 | የመሕ□ት ካርድ | - | | |
| 10 | የመፃሕፍት መደገፊያ□ች | 100 | 13x10 | |
| 11 | ማንበቢያ ጠረጴዛ | 16 | 80x150x74 | |
| 12 | ወንበር | 80 | 35x35x77 | |
| 13 | የካርድ ሣጥን | 1 | 52x44x44 | ባለ 12 መሳቢያ |
| 14 | የኃላፊው ጠረጴዛ | 1 | 80x162x74 | |

| ተ.ቁ | ዓይነት | ብዛት | መጠን በሴንቲ.ሜ/ | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|
| 15 | የመጽሐፍት ማንጓዣ ጋሪ | 1 | 60x100x80 | |
| 16 | የኃላፊው ወንበር | 1 | 40x56x78 | |
| 17 | የጋዜጣ መደርደሪያ | 1 | - | |
| 18 | የመጻሕፍት መደርደሪያ | 1 | 95×40×105 | |
| 19 | የመጻሕፍት ሽልፍ | 1 | 120×40×200 | |
| 20 | ጠመኔ ሰሌዳ | 1 | 500×120 | |
| 21 | ማስታወቂያ ሰሌዳ | 1 | 120×120 | |
| 22 | የግድግዳ ሰዓት | 1 | | |
| 23 | ጠረጴዛ | 1 | | |
| 24 | ፋይል ካቢኔት | 1 | 45×62×35 | |
| 25 | የጠረጴዛ ደወል | 1 | | |
| 26 | ኮምፒውተር | 2 | – | – |

**ማሳሰቢያ፣**

ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ የተካቱት የቤተመጻሕፍት ግብአቶች በዝቅተኛ መጠን የተቀመጡ ሲሆን በትምህርት ቤት ያሉ ተማሪዎች ቁጥር ሲጨምር ግብአቶቹም በዛው ልክ ይጨምራሉ::

### 4.5.7 <u>የICT ማዕከል</u>

ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት መማሪያ ክፍል በተጨማሪ ከትምህርታቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ማግኘት የሚያስችላቸው የICT ማዕከል (የኢንተርኔት አገልግሎት ማዕከል) ሊኖራቸው ይገባል፡፡እስከ 1500 ተማሪዎች ላሉት ት/ቤት በአንድ ጊዜ 40 ተማሪዎችን ማስተናገድ የሚችል አንድ ማዕከል ሊኖረው ይገባል፡፡ነገር ግን የተማሪዎች ብዛት በጨመረ ቁጥር

የICT ማዕከል ብዛትም በዚሁ ስሌት መሰረት ይጨምራል፡፡ የኮምፒውተር ብዛትም ለአንድና ተማሪ አንድ መሆን ይኖርበታል።

4.5.8 የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል

በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ደረጃውን ጠብቆ ተጨባጭ የሆነ ትምህርት እንዲሆን በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መደገፍ አለበት::እነዚህን መሳሪያዎች ገዝቶ ለሟሟላት የትምህርት ቤቱ አቅም ስለማይፈቅድ እነዚህ መሳሪያዎች በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች መሰራት ስላለባቸው ይህንኑ ለማማሏት የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ::በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚገባ መደራጀት አለባቸው::

ከዚህ አኳያ የመማር ማስተማሩን ሂደት ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ለተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በተፈለገው ዓይነትና ጥራት እንዲሁም ብዛት ለማዘጋጀትና ለሟሟላት የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት የሚከተሉት ዕቃዎችና መሳሪያዎች ሊሟሉላቸው ይገባል

4.5.8.1 የቢሮ ዕቃዎች

| የዕቃው ዓይነት | ብዛት |
|---|---|
| ወንበር | 3 |
| ጠረጴዛ | 3 |
| መደርደሪያ ለመሳሪያዎች | 1 |
| መደርደሪያ ለዕቃዎች | 1 |
| የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ | 1 |

4.5.8.2 የእጅ መሣሪያዎች

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | ስክሩ ድራቨር | 2 | |
| 2 | አግድም ቆራጨ መጋዝ | 2 | |
| 3 | የብረት መቁረጫ መጋዝ | 2 | |
| 4 | መላጊያ ትልቁ | 2 | |

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 5 | መላጊያ ትንሹ | 2 | |
| 6 | ተጠቅላይ ሜትር | 2 | ባለ3 ሜትር |
| 7 | ቲ–ስኳር | 2 | |
| 8 | ትራይ ስኳር | 2 | |
| 9 | ድሮዊንግ ኢንስትሩመንት | 8 | |
| 10 | ኘሮትራክተር | 2 | |
| 11 | ትራንግል ሄቪ ፕላስቲክ | 4 | 30፣60፣90 |
| 12 | ትራንግል ሄቪ □□ስቲክ | 4 | 45፣90 |
| 13 | የእንጨት መሰርሰሪያ | 2 | |
| 14 | የእንጨት ሞረድ | 4 | |
| 15 | የወረቀት መቁረጫ | 2 | 61×51 ሳ.ሜ ተለቀ |
| 16 | ትንሽ የእንጨት መሳሪያ ሞርሣ | 2 | |
| 17 | የእንጨት መሮ | 2 | |
| 18 | ሲክላምኘ | 4 | |
| 19 | ፒንሣ | 2 | |
| 20 | መዶሻ | 2 | |
| 21 | ጋሪ | 2 | |

### 4.5.9 የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ

- ተማሪዎች ካላቸው የአካልና የስሜት ማደግ ባህሪያቸው የተነሣ በተለያዩ መንገዶች ለበሽታና ለአደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡
- ክእነዚህም፣
  - ➢ በጨዋታ ሜዳ ላይ እንዲሁም በሥራ ቦታዎች የወለምታ ፤ የስብራት፤ የመቁሰልና የመድማት ፤ የእባብ የመነደፍና በውሻ የመነከስ፤ በስለት ነገር የመቆረጥና የመወጋት፤
  - ➢ በልዩ ልዩ ሕመሞች ምክንያት/ በስኳር በሽታ፣ በሚጥል በሽታ/ አእምሯቸውን የመሳት፤ በውኃ የመስመ□ና የመታፈን ሁኔታዎች
  - ➢ ቆሻሻ ውኃ በመጠጣት የተቅማጥና የተውከት ችግር በተለያየ ምክንያት የደም መመረዝና ትንፋሽ የማጠር ሁኔታዎች ናቸው ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮችን ለመቅረፍ የሕክምና እርዳታ የሚሰሩና በአጠቃላይ በጤና አጠባበቅ /sanitation & hygine/ ላይ ትምህርት የሚሰጥ የጤና ባለሙያ በትምህርት ቤቱ ይመደባል። በአቅራቢያው የጤና አገልግሎት ቢኖርም እንኳን እቦታው እስኪደርስ ድረስ በሽተኛው ሊጎዳ ስለሚችል የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል ትምህርት ቤቱ ሊኖረው ይገባል።

በትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ መስጫ ሣጥን ( first Aid kit ) ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው የሕክምና መሣሪያዎች የሚከተሉት ናቸው ፡፡

1 Adhesive plaster 5cm x10mrollS
2 12 vow gauze bandage 8 cm×5m rols
3 dissecting forceps
4 Examination gloves
5 1 bottle of Dettol 250 ml/alcohol/
6 Scissors 14 cm Gc.P
7 Elastic bandage 10 cmx4.5m
8 2 elastic woven bandage 8 cm×5m
9 12 vow gauze bandage 7 5 cm×5m
10 4 triangular bandages
11 Cotton wool 400 gm
12 1 pack hand plaster ናቸው
13 የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ሳጥን
14 እስትሬቸር /አንድ እስትሬቸር ለ100 ተማሪዎች ስሌት

### 4.5.10 መዝናኛ ክበብ

#### 4.5.10.1 የመምህራንና ሠራተኞች መዝናኛ ክበብ

መምህራንና ሠራተኞች ጠዋትና ከሠዓት በኋላ ባለው የእረፍት ሠዓት እንዲሁም በምሳ ሰዓትና በቀን ውስጥ ባለው ሌላ የእረፍት ጊዜያቸው ሻይ፣ቡና፣ ለስላሳ፣ ቁርስና ምሳ እንዲሁም ራሳቸውን ዘና የሚያደርጉበት መዝናኛ ክበብ በት/ቤቱ ሊኖር ይገባዋል። ክበቡ በአንድ ጊዜ ሁሉንም መምህራንና ሠራተኞች ሊያስተናግድ

የሚችልና ለእንግዶች ሊሆን የሚችል ተጨማሪ ወንበሮችና ጠረጴዛዎችን የያዘና በዋነኛነት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት።

1. 25 ኢንች ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ቴሌቪዥን
2. ሲዲ ማጫወቻና ሊያዝናኑ የሚችሉ ሲዲ ወይም የቪዲዮ ካሴቶች፣
3. የሳተላይት ዲሽ፣
4. አንድ ኢንተርኔት ኔትወርክድ የሆነ ኮምፒዩተር፣ /እንደ አስፈላጊነቱ በመምህራንና ሠራተኞች ቁጥር የሚወሰን/
5. የቤት ውስጥ መጫዎቻዎች፣
    - ዳማ
    - ቼዝ
    - የጠረጴዛ ቴንስ መጫወቻ እና
    - ሌሎች የቤት ውስጥ (Indoor games)
6. ፍሪጅ
7. ለሻይ ለቡና ለምግብ ማዘጋጃ ሊሆኑ የሚችሉ ቁሳቁሶች

### 4.5.10.2 የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ

ተማሪዎች እንደ መምህራንና ሠራተኞች ባላቸው ትርፍ ሰዓት የሻይ፣ ቡና፣ለስላሳ ቀለል ያሉ የምግብ ዓይነቶች የሚዘጋጁበትና ራሳቸውን ዘና የሚያደርጉበት ቢያንስ በአንድ ጊዜ አብዛኛውን የተማሪ ቁጥር ሊያስተናግድ የሚችል የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ ሊኖር ይገባል። ክበቡ በዋነኛነት የሚከተሉት ሊኖሩት ይገባል።

የጠረጴዛ ቴንስ መጫወቻና ከተገኘ ሌሎች የቤት ውስጥ መጫዎቻዎች (indoor games)

### 4. 5 .11 የአዳራሽ አጠቃቀም

- እንደ አስፈላጊነቱ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ የአካባቢው ኅብረተሰብ እየተገናኙ ስለ ትምህርቱ ሂደትና ስለ ት/ቤቱ ዕድገትና መሻሻል የሚወያዩበት መድረክ ፤
- የክፍል ውስጥ ትምህርትን የሚያዳብሩ እንደ፣
    - የጥያቄና መልስ ውድድሮች
    - የተማሪዎች የፈጠራ ሥራዎች ኤግዚቢሽኖች፤
    - የሥነጽሑፍ ፤ ድራማና ሙዚቃ ዝግጅቶች፤

- ክርክር፣ ውይይት ሲምፖዚየምና የተጋባዥ እንግዶች ንግግር
- ከአካባቢ እስከ ዓለም አቀፍ ደረጃ በሚታዩ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ባህላዊና ተፈጥሮአዊ ክስተቶችና ወቅታዊ ጉዳዩች ላይ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲጨብጡና ለችግሮች መፍትሔ እንዲፈልጉ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች የሚዘጋጁበት መሆን አለበት፡፡

- በአጠቃላይ አዳራሹ በከፍተኛ ወጪ የተሠራ በመሆኑ ለመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ አስተዋፅኦ በሚሰጥ መንገድ አገልግሎት ላይ ሊውል ይገባል፡፡

## 4.6 **ለየትምህርት ዓይነቱ** የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

- በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት አሳታፊና ተማሪ ተኮር እንዲሆን የትምህርት መሣሪያዎች በዓይነትም ሆነ በብዛት መገኘት ለትምህርት ጥራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ተማሪዎች በንድፈ ሀሳብ የተማሩትን ትምህርት በተግባር ማለትም የትምህርት መሳሪያዎችን በመዳሰስ፣ በመፈተሽና በመለካት ከተማሩ ትምህርቱን በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ። በመሆኑም በፋብሪካ የተመረቱ የትምህርት መሳሪያዎች ተገዝተው ወይም ይህ በማይገኝበት ወቅት መምህራንና ተማሪዎች በትምህርት ማዕከላት ተገኝተው በመስራት ማቅረብ አለባቸው፡፡

በአንዳንድ የትምህርት ዓይነቶች በፋብሪካ ተሠርተው በገበያ ላይ የሚገኙ የትምህርት መሣሪያዎች ዝርዝር በአባሪነት ተያይዟል፡፡

### 4.6.1 **ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች**

ማየት ለተሳናቸው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

- የብሬል ወረቀት
- ስሌትና ስታይልስ
- በብሬል የተጻፈ የመደበኛ ትምህርት መጽሐፍ ኮፒ
- አባከስ
- ቴሪኮርደርና ካሴት
- የታይፕ መኪናና የቴኘሪኮርደር መለዋወጫ
- ነጭ ብትር/ዘንግ
- ማየት የተሳናቸው ለንባብ የሚረዱበት መሣሪያ /

መጠነኛ የዕይታ **ችግር ላለባቸው**

- በቅርበት የሚያሳይ ቴሌቪዥን
- አቮርሄድ ኘሮጄክተር
- ትላልቅ ስፒል
- ባለ ትልቅ መስመር ወረቀት
- አጉሊ መነጽር
- ለማንበቢያ የሚረዳ
- የታይኘ መኪናና ቴኘሪከርደር

መስማት ለተሳናቸው

- መሣሪያዎች መንቀሳቀሳቸውን የሚያመለክት ብርሃን ማሣያ መሣሪያ፡
- የማስጠንቀቂያ ደወል ለመተካት እንደባትሪ ያለ ነገር እንዲታይ ማድረግ በከፊል ለሚሰሙት ድምጽ አጉሊ መሣሪያ መጠቀም ለምሳሌ ረዳት የመስሚያ መሣሪያ
- የታይኘ መኪና

**መጠነኛ የእይታ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች**

- የዕይታ መሣሪያዎች፤ ብርሃን አስተላለፊ ወረቀት ፊልሞች ካብሽን፤ ስላይድ ፊልሞችና ቻርት ለማሳያ አስፈላጊ ናቸው ::

4.7. የተማሪ መፅሐፍት ጥምርታ

- የተማሪ መጽሃፍት ተሟልቶ መገኘት ለትምህርቱ ጥራት እጅግ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የተማሪ መፅሃፍ ጥምርታ አንድ ለአንድ መሆን አለበት።

4.8. የተማሪ ክፍል ጥምርታ

- የተማሪ ክፍል ጥምርታ ለትምህርት ጥራት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ፡ ከ9ኛ –12ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በአንድ ክፍል 40 /1:40/ ይመደባሉ፡፡

4.9. የሰው ኃይል ምደባ

- የትምህርት ሥራ በጥራትና በተፈለገው መንገድ ሊካሄድ የሚችለው ት/ቤቱ በየትምህርት ዓይነቱ የሚሰጡ ትምህርቶች ለደረጃው የሰለጠኑ መምህራን

እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በጥራትና በበቂ ሁኔታ አሟልቶ ሲገኝ ነው። ስለሆነም

- በ2ኛ ደረጃ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ሳይክል የሚመደቡ መምህራን ዲግሪ ያላቸው ሆነው የማስተማር ሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው ይሆናሉ፡፡
- አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለሚከተሉት መሰረታዊ የሥራ መደቦች ብቁ መምህራንና ሠራተኞች ሊኖረው ይገባል፡፡

4.9.1 **የመምህራንና ሠራተኞች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ**

| ተ.ቁ | የሥራው መስክ | ብዛት | ለሁለተኛ ደረጃ /9-12/ የትምህርት ደረጃ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1ኛ ሳይክል /ከ9ኛ-10ኛ/ | 2ኛ ሳይክል /11-12/ | ምርመራ |
| 1 | ርዕሰ መምህር | 1 | ኤም.ኤ/ኤምኤስሲ/አማራጭ/ | ኤም.ኤ/ኤምኤስሲ | ከሰለጠኑበት ትምህርት በአንዱ በትምህርት አስተዳደር ሆኖ የርዕመም/ር ሥልጠና የወሰደ/ች |
| 2 | ምክትል ርዕሰ መምህር | 1 | ኤም.ኤ/ኤምኤስሲ | ኤም.ኤ/ኤምኤስሲ | ከሰለጠኑበት ትምህርት በአንዱ በትምህርት አስተዳደር ሆኖ የርዕ መም/ |ሥልጠና የወሰደ/ች |
| 3 | መምህር | | ቢ.ኤ/ቢ.ኤስሲ | ኤም.ኤ/ ኤም.ኤስሲ | እንደ የክፍሉ ብዛት የሚታይ ሆኖ እስከ 18 ክፍለ ጊዜ ይይዛል፡፡ |
| 4 | የካውንስሊንግ ባለሙያ | 1 | ቢ.ኤ/ቢ.ኤስሲ | ቢ.ኤ/ቢ.ኤስሲ ወይም በላይ | በትምህርት ሳይኮሎጂ የተመረቀ/ ች |
| 5 | አስተዳዳርና ፋይናንስ | 1 | ቢ.ኤ | ቢ.ኤ | በትምህርት አስተዳደር ወይም በማኔጅመንት የሰለጠነ/ች |
| 8 | ሂሳብ ሠራተኛ; | 1 | ዲፕሎማ | ዲፕሎማ ወይም በላይ | በሂሳብ አያያዝ የተመረቀ//ች |

| ተ.ቁ | የሥራው መስክ | ብዛት | ለሁለተኛ ደረጃ /9-12/ የትምህርት ደረጃ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1ኛ ሳይክል /ከ9ኛ-10ኛ/ | 2ኛ ሳይክል /11-12/ | ምርመራ |
| 9 | ገንዘብ ያዥ | 1 | ዲፕሎማ | ዲፕሎማ | በሂሳብ አያያዝ የሰለጠነ/ች |
| 10 | ንብረት ክፍል ኃላፊ | 1 | ዲፕሎማ | ዲፕሎማ | በንብረት አያያዝ የሰለጠነ/ች |
| 11 | ፀሐፊ | 1 | ዲፕሎማ | ዲፕሎማ | በሴክሬታሪያት ሳይንስ የሰለጠነ/ች |
| 12 | የተማሪዎች መረጃ ኃላፊ | 1 | ዲፕሎማ | ዲፕሎማ | በመዝገብ አያያዝ የሰለጠነ/ች |
| 13 | የቤተ መጻሕፍትኃላፊ | 1 | ቢኤቢኤስሲ | ቢኤቢኤስሲ | በላይብረሪ ሳይንስ የሰለጠነ/ች |
| 14 | የላብራቶሪ ቴክኒሻን | 1 | ዲፕሎማ | ዲፕሎማ | በሳይንስ ትምህርት የሰለጠነ/ች |
| 15 | ጽዳት ሠራተኛና ተላላኪ | 1 | 12ኛ | 12ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀ/ች | እንደ ተማሪውና ክፍሉ ብዛት የሚወሰን |
| 16 | የጥበቃ ሠራተኛና አትክልተኛ | 4 | 12ኛ | 12ኛ | እንደ ተማሪውና ክፍሉ ብዛት የሚወሰን |
| 19 | በቀይ መስቀል የሰለጠነ | 1 | በቀይ መስቀል የሰለጠነ | በቀይ መስቀል የሰለጠነ | እንደተማው ብዛት የሚጨመር ይሆናል |

### 4.9.2 የልዩ ትምህርት መምህራንና ሠራተኞች ድልድል

1.መምህር--------------------በዲግሪ የተመረቀ/ችና የልዩ ትም/ሥልጠና የወሰደ/ች

2. የንግግር ወጌሻ-----------------ከከፍተኛ ትም/ተቋም በዲፕሎማ የተመረቀ/ችና የልዩ ትም/ሥልጠና የወሰደ/ች

በመደበኛ ት/ቤት የመምህራንና ሠራተኞች ድልድል እንደተጠበቀ ሆኖ፤

በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ከ10–20 ለሚሆኑት ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት ለሚከፈት ልዩ ክፍል የሚያስፈልገው ተጨማሪ የሰው ኃይል እንደሚከተለው ይሆናል ፡፡

- ማየት ለተሳናቸው ሕፃናትና ወጣቶች አንድ ልዩ መምህር፤
- መስማት ለተሳናቸው ሕፃናትና ወጣቶች አንድ መምህር፤
- የአእምሮ ዕድገት ዝግመት ላለባቸው ህጻናት አንድ መምህር፤
- የስሜት መረበሽ ላጋጠማቸው አንድ ልዩ መምህርና የሳይኮሎጂስት ባለሙያ ፤
- የመማር ችግር ላለባቸው አንድ ልዩ መምህር
- የመናገር ችግር ላለባቸው አንድ ልዩ መምህር ወይም የአንደበት ወጌሻ
- የአካል ጉድለት ላለባቸው አንድ ረዳት መምህር
- ተደራራቢ ችግር ላለባቸው ህጻናት እንደ ሁኔታው ታይቶ የሰው ኃይል ይመደባል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሕፃን የመስማትና የማየት ጥምር ችግር ካለበት የሰው ኃይል ምደባው አንድ ባለሙያ ለአንድ ወይም ለሁለት ሕፃን ይሆናል፡፡
- ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው ሕፃናት የሚመደበው ባለሙያ እንደ ሕፃናቱ የአእምሮ ችሎታና ልዩ ተሰጥኦ ሁኔታ ይለያያል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሕፃን በሒሣብ ትምህርት ወይም በሥዕል ከሌሎች ሕፃናት በጣም የመጠቀ ችሎታ ካለው በዚህ ትምህርት እንዲገፋበት የሚመለከተውና ችሎታ ያለው መምህር ተመድቦለት እንዲከታተለውና እንዲያበረታታው ይደረጋል
- ልዩ ፍላጎቶች ያሏቸው ሕፃናትና ወጣቶች ከሌሎች መደበኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው እንዲማሩ በሚደረግበት ጊዜ የተለየ ክህ□ት እንዲያገኑ፣ ለማድረግ ከመደበኛ ክፍሎችና የትምህርት ጊዜ ውጪ በልዩ ፕሮግራም / Unit / በልዩ መምህራንና ባለሙያዎች ይረዳሉ□

5. የማስተማሪያ ዘዴ

የማስተማር ዘዴዎች የእያንዳንዱን ተማሪ የትምህርት አቀባበልና አፈፃፀም እንዲሁም የመረዳት ግንዛቤ መሠረት ያደረገ መሆን ስለሚገባው መምህሩ የተማሪውን ዕውቀትና የመረዳት ችሎታ መሰረት ያደረገና ተማሪው ነፃ ሆኖ የመጠየቅና የመመለስ ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚያስችለውን የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም አለበት። ስለሆነም መምህሩ

የሚጠቀመው የማስተማሪያ ዘዴ በዋነኛነት ተማሪውን ማዕከል ያደረገ (studnt centered) አሳታፊ ማስተማር ሊሆን ስለሚገባው የሚከተሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች መጠቀምና ማጎልበት ይኖርበታል።

1. የጥያቄና መልስ (Question and Answer) 5/ የሚና ጨዋታ (Role playing)
2. ውይይት (Group Discussion) 6/ እንግዳ መጋበዝ Guest Invitation
3. ስዕላዊ ማብራያ (Illustration) 7/ ፕሮጀክት ሥራ Project Work
8/ simulation መስሎ መጫወት
4. የአንድ ጉዳይ ጥናት (Case Study ) 9/ ወዘተ

ከላይ የተጠቀሱትንና ተዛማጅ የሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ውጤታማ ለማድረግ መምህሩ ተማሪዎች በነፃነት በመማር ማስተማር ስራው እንድ አካል እንደሆኑ ለማሳወቅ እንዲሁም ንቁና ብቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የራሱን ተነሳሽነትና ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

6. የሁለተኛ ደረጃ መምህር ፕሮፋይል

- የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ስለሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት፣የክፍል ውስጥ አመራርና የመማር ማስተማር ሂደት አያያዝ፣የተከታታይ ምዘናና ግምገማ አፈጻጸም፣በትምህርት ዙሪያ ጥናትና ምርምር በማካሄድና ችግር ለመፍታት አዳዲስ ሀሳቦችን በማፍለቅ፣ ከትምህርት ቤቱና ከአከባቢ ህብረተሰብ ጋር ግንኙነት በመፍጠር የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ያደርጋል፣
- የሁለተኛ ደረጃ መምህራን በተማሪዎቻቸው መካከል ሊኖሩ ስለሚችሉ ልዩነቶች ማለትም የትምህርት አቀባበል ችሎታና ፍላጎት በመገንዘብና ሳይንሳዊ የአቀራረብ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን ለጥሩ ውጤት ያበቃል፣
- በፆታ፣በዘር፣በኃይማኖት እንዲሁም በአካል ጉዳት ወይም በችሎታ ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ለተማሪዎች ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት፣ የትምህርት ፍትሃዊነት ያረጋግጣል።
- በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ከአካባቢያዊ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘበ ትምህርት በመስጠት የሚገኝ

ዕውቀትና ችሎታ ኖሮት ተማሪዎችን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ በደረጃቸው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡

6.1 **ከሁለተኛ ደረጃ መምህር የሚጠበቅ** ባህሪ

- የሁለተኛ ደረጃ መምህርነትን ሙያ የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር የመፍጠርና የማዳበር፣ ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በጋራ የማቀድ፣የመስራት፣ችግሮችን በጋራ የመፍታት፣ ሙያውን የማሳደግ፣በህብረተሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግና ኃላፊነትን ይሸከማል፣
- በክፍል ውስጥ ገዋን ሁለጊዜ ለብሶ መገኘት ይኖርበታል።
- ህገመንግሰቱን የማክበር፣ የዲሞክራሲ መርሆዎችን የመተግበር፣ ሴት ተማሪዎችን የመደገፍና የማበረታታት ባህል ማዳበር፣
- በትምህርት ቤት ውስጥ ለተማሪዎች የመልካም ሥነ ምግባር ቀዳሚ አርአያ ሆኖ ይገኛል፡፡
- ለት/ቤቱና ለሚኖርበት ማኅበረሰብ መልካም አርአያ ሆኖ ይገኛል፡፡
- በክፍል ውስጥ የመማር ሂደት በሚካሄድበት ወቅት ሞባይልና ሌሎች አዋኪ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ከመጠቀም ይቆጠባል ።

7. **የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ባህሪ**

➢ **የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ያጠናቀቀ ተማሪ** (9-10)

- በአካልና በአእምሮ ብስለት ለሥራ ብቁ ነው፣
- ራሱንና አከባቢውን ከማህበራዊ ጠንቆችና ጎጂ ባህሎች ለመከላከል የሚያስችል ዝግጅት አለው፡፡
- መብቱን ለመጠበቅና ግዴታውን ለመወጣት ዝግጁ ነው፡፡
- አዳዲስ ማሽኖችና መሣሪያዎችን ለማንቀሰቀስና ለመጠቀም የሚያስችል መሰረታዊ ዕውቀት አለው፡፡
- መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ትምህርት አማካይነት የዳበረ የተግባርና የንድፈ ሃሳብ ዕውቀቶች ለማግኘት ዝግጁ ነው፡፡
- በትም/ቤቱ ቅጥር ግቢ የትም/ቤቱን ዩኒፎርም ለብሶ መገኘት ይገባዋል።

➢ **የሁለተኛ ደረጃ የቀለም ትምህርትን ያጠናቀቀ ተማሪ** (11-12)፣

- ኃላፊነትን በሚጠይቁ ሥራዎች ለመሰማራትና የከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል የሚያስችል ዝግጅት አለው፡፡
- አጫጭር ሥልጠናዎች ከተሰጠው በማንኛውም የሥራ መስክ ተሰማርቶ መስራት ይችላል፡፡
- ህጋዊ ለሆኑ ጉዳዮች የውክልና ኃላፊነት የመሸከምና በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በሚደረጉ ሕጋዊ ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ ብቃት አለው፡፡
- በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ የትምህርት ቤቱን ዩኒፎርም ለብሶ መገኘት ይገባዋል።
- በክፍል ውስጥ ሞባይልና ሌሎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ሊያውኩ የሚችሉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን ከመጠቀም ይቆጠባል።

8. የማስተማር መማር ሂደት መመሪያዎችና ሰነዶች

- የሥ/ትምህርት ማዕቀፍ፣
- ሥርዓተ ትምህርት፣
- የመምህሩ መ□ሪያዎችና ማስተማሪያ መጻሕፍት በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣
- የክፍለ ጊዜ ስርጭት፣
- የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል መመሪያ፣
- የዘመኑ የትምህርት ካሌንደር፣
- የቤተ ሙከራ አደረጃጀት፣ አያያዝና አጠቃቀም ማኑዋል::

8.1 **የትምህርት አመራርና አስተዳደር** መመሪያዎች አጠቃላይ መመሪያዎች

- ስርአተ ትምህርት ማዕቀፍ፣
- የየትምህርት ዓይነት፣
- የመምህሩ መ□ሪያዎችና መረጃ መፅሐፍት በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣
- የተማሪው መፅሐፍ በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣
- በመደበኛ ትምህርት የተዘጋጁት እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም፣
- ት/ቤትን መሠረት ያደረገ አመራር መመሪያ፣

(School Based Management Manual)

- የተማሪዎች ካውንስል አደረጃጀት መመሪያ፣

- የተጓዳኝ ትምህርት አደረጃጀት መመሪያ፣
- በመደበኛ ትምህርት የተዘጋጁት እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም
    - የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርህ ግብር እስትራቴጂ።

ሌሎች ልዩ ልዩ መመሪያዎች

- የአጠቃላይ ትምህርት አመራር አደረጃጀትና የህብረተሰብ ተሳትፎ የፋይናንስ መመሪያ(Blue Book)፣
- አጠቃላይ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ፣
- የአርብቶ አደር አካባቢ ትምህርት እስትራቴጂ፣
- ስለግል የትምህርት ተቋሞች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብና ማብራሪያ፣
- አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት፣
- የማዕከልና የክልል አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 41/85፣
- የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል መመሪያ(ቀድሞ የተዘጋጀው)፣
- የትምህርት ቤቶች ተጨማሪ በጀት መመሪያ(School Grant Manual)፣
- አገር አቀፍ የሴቶች ትምህርት እስትራቴጂ፣
- የመምህራን ልማት ፕሮግራም ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣
- የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራም ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣
- የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ፣
- የስነዜጋና ስነምግባር ትምህርት ፕሮግራም መመሪያዎች፣
- የትምህርት ህግ።

## 9. የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት

ዓላማ፡

- በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል (9-10) የሚሰጠው ትምህርት ተማሪዎች ባላቸው ፍላጎትና ችሎታ መሰረት ዕውቀታቸውና ክህሎታቸው በማዳበር ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ ማዘጋጀት፣

- የሁለተኛ ደረጃ 2ኛ ሳይክል (11-12) የሚሰጠው ትምህርት ተማሪዎች በመረጡት የትምህርት መስክ ለከፍተኛ ትምህርት የሚያበቃቸውን በቂ ችሎታና ክህሎት እንዲጨብጡ ለማስቻል፡፡

  በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው የትምህርት ፕሮግራም የሚከተሉትን ነጥቦች ሊያካትት ይችላል፡፡

  1. የትምህርት ኘሮግራም እርዝመት፣
  2. የአየር ፀባዩ / ክረምት/፣
  3. ብሔራዊ በዓሎች፣
  4. የትምህርት ዓይነቶች ብዛት፣
  5. የሲለበስ ስፋት፣
  6. በቀን ውስጥ የሚመደበው የትምህርት ሰዓት ርዝመት፡፡

**በዚህ መሰረት፣**

- ትምህርት የሚሰጠው በሙሉ ቀን ፕሮግራም ነው፡፡
- በየደረጃው የሚሰጠው ትምህርት ከ203-206 ባሉት ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ታስቦ የተዘጋጀ ነው የትምህርቱም ወቅት በዓመት ውስጥ በሁለት ሴሚስተር ወይም በሶስት ተርም ተከፍሎ ይሰጣል፡፡
- በሳምንት አምስት የማስተማሪያ ቀናት ይኖራሉ..'.
- በቀን ውስጥ የሚመደበው ክፍለ ጊዜ ሰባት ነው፡፡ የክፍለ ጊዜ ርዝማኔም 45 ደቂቃ ይሆናል፡፡
- በመጀመሪያው ሳይክል አጠቃላይ ትምህርት ይሰጣል
- በሁለተኛው ሳይክል የሚሠጠው ትምህርት በስፔሻላዜሽን ነው

የሙሉ ቀን ኘሮግራም መደራጀት **አስፈላጊነት** –

- ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት የሚመጣበትን የቦታው ርቀት እየታየ የእለቱን ትምህርት የመጀመሪያውና የመጨረሻ ጊዜ እንደ አመቺነቱ መወሰን ያስችላል፡፡
- በቀን ትምህርት ኘሮግራም እስከ ሰባት ክፍለ ጊዜ መስጠት ያስችላል፡፡

– የያንዳንዱን ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ ከ40–45 ደቂቃ በማድረግ የተረጋጋ የማስተማር መማር ሂደት መፍጠር ያስችላል።

– በክፍለ ጊዜው የተለያዩ የትምህርት መሳሪያዎችን፣ የማስተማሪያና የመገምገሚያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ በተሻለ ሁኔታ ማስተማር ያስችላል።

– እናሳ ክፍለ ጊዜ ለተሰጣቸው ትምህርቶች ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ ማግኘት ያስችላል።

– ለተማሪዎች፣ የክፍል ሥራና የቤት ሥራን በመስጠት ሥራቸውን የመከታተል የማረምና ደከም ላሉ ተማሪዎችም ድጋፍ ለመስጠት ያስችላል፡፡

– ተማሪዎችና መምህራን ቤተመጻሕፍት፣ ትምህርት ማበልጸጊያ ማእከል፣ ላቦራቶሪ፣ ወርክሾፕ ወዘተ እንዲገቡና እውቀታቸውንና ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ያስችላል።

9.1. የትምህርት ዓይነቶችና የክፍለ ጊዜ ስርጭት

9.1.1. በመጀመሪያ ሳይክል /9–10/ የሚሰጡ የትምህርት አይነቶችና የክፍለ ጊዜ ብዛት ፣

| ተ.ቁ | የትምህርት መስክ | የትምህርት ዓይነት | የሳምንት የክፍለ ጊዜ ስርጭት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 9 | 10 |
| 1 | ቋንቋዎች | እንግሊዘኛ | 4 | 4 |
| | | አማርኛ | 2 | 2 |
| 3 | የተፈጥሮ ሳይንስ | ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ | 2 | 2 |
| | | ፊዚክስ | 3 | 3 |
| | | ኬሚስትሪ | 3 | 3 |
| | | ባዮሎጂ | 3 | 3 |
| 4 | የኅብረተሰብ ሣይንስ | ሥነ–ዜጋ | 3 | 3 |
| | | ጂኦግራፊ | 2 | 2 |
| | | ታሪክ | 2 | 2 |
| 5 | የሰውነት ማጎልመሻ | የሰውነት ማጎልመሻ | 1 | 1 |

ማሳሰቢያ፣

ከላይ የተገለፀው የፈረቃ ክ/ጊዜ ሥርጭት ሲሆን ትምህርቱ በሙሉ ቀን ሲሰጥ ክፍለ ጊዜው ወደ 35 ከፍ ይላል፡፡ አምስቱ ተጨማሪ ክፍለ ጊዜያት አንዱ ለእንግሊዘኛ፣ ሦስቱ ክ/ጊዜያት ለሦስቱ ሳይንሶች እና አንዱ ለሰውነት ማጉልመሻ ትምህርት ይመደባሉ፡፡

9.1.2. *በ2ኛ ሳይክል /11–12/ የሚሰጡ የትምህርት አይነቶችና የክፍለ ጊዜ ብዛት ፣*

| ተ.ቁ | የትምህርት መስክ | የትምህርት ዓይነት | የሳምንት የክፍለ ጊዜ ስርጭት | |
|---|---|---|---|---|
| | | | 11ኛ | 12ኛ |
| 1 | የተፈጥሮ ሳይንስ | **ልዩ ኮርሶች /Specialized/** | | |
| | | 1. ፊዚክስ | 4 | 4 |
| | | 2. ኬሚስትሪ | 4 | 4 |
| | | 3. ባዮሎጂ | 4 | 4 |
| | | 4. ቴክኒካል ድሮዊንግ | 2 | 2 |
| 2 | | **የጋራ ኮርሶች/COMMON CO,/** | | |
| | | 1. እንግሊዘኛ | 6 | 6 |
| | | 2. ሂሳብ | 5 | 5 |
| | | 5. ሥነ–ዜጋ | 3 | 3 |
| | | 6. የሰውነት ማጎልመሻ | 1 | 1 |
| | | 7. ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ | 3 | 3 |
| | | **ልዩ ኮርሶች /SPECIALIZED/** | | |
| 3 | የኅብረተሰብ ሣይንስ | ኢኮኖሚክስ | 4 | 4 |
| | | ጂኦግራፊ | 4 | 4 |
| | | ታሪክ | 4 | 4 |
| | | ቢዝነስ /Generas Business/ | 2 | 2 |
| 6 | | አማራጭ ኮርሶች /Elective/ | | |
| | | አንድ የብሔረሰብ ቋንቋ ወይም አማርኛ | 3 | 3 |
| 7 | **የሳምንቱ ጠቅላላ ፔሬድ ብዛት** | | 35 | 35 |

በልዩ ትምህርት የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች፣

በእርከኑ በመደበኛ ት/ቤቶች የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪ የሚሰጡት የተለዩ ትምህርት ይዘቶች የሚከተለት ናቸው፡፡

የመስማት ጉድለት ላለባቸው

የምልክት ቋንቋ መሪ የማስተማሪያ ቋንቋ ይሆናል።

ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሚሰጡ

- የነፍስ ወከፍ ንግግር
- የቋንቋ ችለታን ማዳበር
- የቡድን ንግግር
- የምልክት ቋንቋ
- የማዳመጥ ሥልጠና

10. የትምህርት ወቅት

- አንድ የትምህርት ዓመት ከ203–206 የትምህርት ቀናት ይኖሩታል፡፡
- አንድ የትምህርት ዓመት በሁለት ሴሚስተሮች ይከፈላል፡፡
- በአንድ ሳምንት ውስጥ አምስት የትምህርት ቀናት ይኖራሉ ፡፡
- በየሴሚስተሩ መጨረሻ የሚሰጡ ፈተናዎች በ10 ቀናት ውስጥ እንዲያጠናቅቁ ይደረጋል፡፡
- በየሴሚስተር መጨረሻ ከፈተና በኋላ የአንድ ሳምንት የፈተና ማረሚያና ውጤት □ማጠ□□□ ጊዜ ይኖራል፡፡

10.1 የትምህርት ቤት ሰዓት

መደበኛ ትምህርት በተመለከተ

- ትምህርት ቤቶች ሙሉ ቀን የሚያስተምሩ ሆኖ በቀን ሰባት ክፍለ ጊዜ እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ 45 ደቂቃ የሚወስድ ይሆናል፡፡ ሆኖም በፈረቃ ለሚሰሩ ትምህርት ቤቶች በቀን 6 ክፍለ ጊዜ እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ 40 ደቂቃ ይኖረዋል፡

የመምህራን የሥራ ሰዓትና አጠቃቀም

- የአንድ መምህር የሳምንት መደበኛ የሥራ ሰዓት 40 ሰዓት ይሆናል፡፡

- ➢ **አንድ መምህር የሳምንቱን የሥራ ሰዓት በሚከተለው መልክ ሊደለድል ይገባዋል፣**

- በክፍል ማስተማር ሥራ ላይ እስከ ሃያ ሁለት ተኩል ሰዓት፣
- በክፍል ትምህርቶች ዝግጅትና የተማሪዎችን ሥራ ለማረምና ለመከታተል እስከ አስራ አንድ ሰዓት ተኩል፣
- ለተጓዳኝ ትምህርት እስከ ሦስት ሰዓት እና
- ለልዩ ልዩ ሥራዎች እስከ ሦስት ሰዓት  መጠቀም ይችላል፡፡

## 10.2 የተጓዳኝ ትምህርት ፤

- ፕሮግራሙ በትምህርት ቤቱ ዕቅድና አቅም መሰረት በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ትምህርቶች በሚያግዝ መልኩ ከክፍል ውጪ የሚሰጥ ሲሆን  ልዩ ልዩ ክበባት እና ሌሎች ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች በማቋቋም ተማሪዎች ባላቸው ዝንባሌ፣ፍላጎትና ችሎታ እንዲደራጁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ተማሪዎች እንደፍላጎታቸው በተለያዩ ክበባት እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ ከተደረገ ትርፍ ጊዜያቸውን ጠቃሚ በሆነ ሥራ እንዲያውሉ በማድረግና እንደፍላጎታቸው በማራዘም ሆነ በማሳጠር የመስራት ዕድል ስለሚያገኙ በክፍል ውስጥ ያገኙትን ዕውቀትና ክህሎት ያዳብራሉ፡፡በሌላ በኩል  በትምህርት ቤት ቆይታቸው  ከጓደኞቻቸው ሆነ  ከመምህራኖቻቸው በሚያገኙት ልምድ፣ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከሚሰጥ መመሪያና በትም/ቤቱ በሚደረጉ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች የወደፊት ዝንባሌያቸውን ሊያዳብሩላቸው የሚችሉ ክህሎቶችን ማግኘት ይችላሉ::
- ስለሆነም ለመማር ማስተማር ሂደት የሚሰጠው ፋይዳ ግምት ውስጥ በማስገባት የተማሪዎች እድገትና ጥንካሬ እየታየ በሳምንት ከ4 ሰዓት በማይበልጥ ውስጥ ፕሮግራሙ መካሄድ አለበት፡፡

**የፕሮግራሙ ዓላማ :–**

- ተማሪው የበለጠ ዕውቀት እንዲገበይ መርዳት፣
- ለሙያ ሥራ አክብሮትና መልካም አርአያነትን ለመፍጠር፣

- ተማሪዎች በፍላጎታቸው በችሎታቸውና በሀገሪቱ የት/ዓላማ መሠረት የወደፊቱን የሙያ መስክ ለመምረጥ እንዲችሉ ለመርዳት፣
- በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀት ችሎታቸውን ለማዳበር፣
- የሥራ መውደድ ባህርይ ለመፍጠርና ለማዳበር፣
- የተማሪዎች ዝንባሌ ወደ ጥናትና ምርምር እንዲያመሩ ለመርዳት፣
- ተማሪዎች ማኅበራዊ ግልጋሎቶችን እንዲሰጡ ለማበረታታት
- በክፍል ውስጥ ትምህርት ብቻ ሊገኙ የማይችሉ ለምሳሌ የማቀድ፣ የመምራት የማስተባበር፣ የመገምገም፣ ኃላፊነትን የመቀበል ፣ ውሣኔ የመስጠትን ፣ ችግሮችን በራስ አነሳሽነትና በፈጠራ የመፍታትን ተግባራትና ክህሎቶችንና ልምዶችን ለማዳበር፤
- ትርፍ ጊዜያቸውን ትምህርት በሚሰጡ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲያሳልፉ በማድረግ፣ እያንዳንዱ ተማሪ በቡድንና በግል የፈጠራ ሥራዎችን እንዲሠራ ለማበረታታት ፤
- ተጨማሪ ደስታና ልዩ ስሜትን በመፍጠር በት/ቤቶቻቸው ላይ ፍቅር እንዲያድርባቸውና የባለቤትነት መንፈስን እንዲገነቡና በዲስኘሊን እንዲታነፁ ማድረግ፤
- በጥልቀትና በስፋት እንዲሰጡ የሚደረጉ የት/ዓይነቶች አማካይነት ለሚደክሙ ተማሪዎች ልዩ እርዳታ ለመስጠት፤
- በአካባቢያዊ / ክልላዊ አገራዊ፤ ዓለም አቀፋዊ የሆኑ ሀገራዊ ጉዳዩችን አዳዲስ ክስተቶችንና ችግሮችን፤ እንዲሁም ግኝቶችን ለተማሪዎች ለማስተዋወቅና . . በመፍትሔ ሰጪነት ለማሳተፍ ነው
- ተማሪዎች የዲሞክራሲ ባህል እንዲያዳብሩ፣ መብታቸውንና ግዴታቸውን አውቀው ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማደረግ፣

11. **የመረጃ አያያዝና ፍሰት**

አንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመረጃ አያያዝና ፍሰት በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡፣

- የትምህርቱ እንቅስቃሴ ምን ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚጠቁም ሪፖርት ለትምህርቱ ስርዓት ባለድርሻዎች (ለተማሪዎች፣ ለት/ቤቱ ማህበረሰብ፣ ለወላጆች ለሕብረተሰቡ፣ ለወረዳ ት/ጽ/ቤት. . .) ቢያንስ በየሩብ አመት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

- የተማሪዎች፣የመምህራን እና የንብረት ጉዳዮችን የተመለከቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፡፡
- ቀበሌ፣ወረዳ ወይም ዞን እና የክልል ትምህርት መዋቅሮች እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ትምህርት ሚኒስቴር ከትምህርት ቤቱ የሚፈልገውን መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡፡
- የተማሪዎችን፣ የመምህራንንና የንብረት መግለጫዎችን በመዝገብ አደራጅቶ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡፡
- የትምህርት ሥራ ሂደት ለመገምገምና ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት ከክልል፣ ከወረዳ ወይም ከዞን እንዲሁም ከማዕከል ወደየተቋማቱ ለሚመጡ የትምህርት ባለሙያዎች ትምህርት ቤቱ የተፈለገውን መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

12. የትምህርት ደረጃ ምዘናና ማጠናቀቂያ መረጃ

ማንኛውም ት/ቤት በአግባቡ የእያንዳንዱን ተማሪ የመማርና በትምህርቱም ለውጥ/እድገት/ ማምጣቱን የሚያመለክቱ መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን መለካት አለበት። ተማሪው ትምህርት ለመማሩ የሚቀርበው መረጃ የሥርዓተ ትምህርቱን ብቃት፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ ሙያዊ እድገትንና ደጋፊ አገልግሎቶችን ለመገምገምና ለማሻሻል ይረዳል። ተማሪው በትምህርቱ የሚያሳየው መሻሻልና አፈፃፀም በዋነኛነት በተማሪው ወላጆችና በት/ቤቱ ማህበረሰብ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በአካባቢው ማህበረሰብ መታወቅ ስላለበት በትክክለኛው መንገድ፣ ግልፅና በአግባቡ ተጠናቅሮ መገለፅ አለበት።

ምዘናን በተመለከተ ለሁሉም ት/ቤቶች የስታንዳርድ አመላካቾች የሚከተሉት ናቸው።

- የት/ቤቱ አመራርና ሠራተኛ ለተማሪዎች ትምህርት ቁርጠኛ መሆን፣ ተሳታፊ መሆንና ተጠያቂነት ሊኖረው ይገባል።
- የተማሪው ትምህርት አቀባበል በአገሪቱ ባለው ሥርዓተ ትምህርትና የማስተማር እንቅስቃሴ ላይ መሠረት ያደረገ መሆን ይገባዋል።
- የተማሪው ውጤት ለት/ቤቶች በሚመደብ ሃብት ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚጠቅሙ መሆን አለበት።

– የምዘና ዘዴዎችና ይዘቶች የተማሪዎቹን ህብረተሰባዊ፣ ስሜታዊ፣ አካላዊና የግንዛቤ/ቋንቋ ግቦችን ማካተት ይኖርባቸዋል።

– ምዘናዎች የእያንዳንዱን ተማሪ ልዩ ፍላጎቶችና ልምዶችን ማንፀባረቅ አለባቸው።

– የተማሪው ቤተሰቦች የተማሪውን ውጤት በተመለከተ ጠቃሚ የመረጃ ምንጮች ተደርገው መወሰድ አለባቸው፡.

– የተማሪዎችን የትምህርት እንቅስቃሴና አፈፃፀምን በተመለከተ ከተማሪው ወላጅ ጋር የሚደረገው የመረጃ ልውውጥና ግንኙነት መደበኛ፣ ጠቃሚና ትርጉም ያለው መሆን አለበት።

– የምዘና ውጤቶች የተማሪው ቤተሰብ ለተማሪው ለሚሰጠው ማንኛውም እስተዋፅኦ መሠረት በመሆናቸው እነዚህ መዛግብቶች በአግባቡ መጠበቅ አለባቸው።

– ተማሪዎች ለየክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ትምህርት በተወሰነው የክፍል ጊዜና የትምህርት ወቅት ተገኝተው መማራቸውን ትምህርት ቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡፡

– ት/ቤቱ ተማሪዎች ተከታታይ ምዘናና የማጠቃለያ ፈተና መውሰዳቸውንና በወቅቱ ባለው መመሪያ መሠረት ወደሚቀጥለው ክፍል ለመግባት የሚያስችልና የነበሩበትን ክፍል አጠናቀዋል የሚል አጥጋቢ ውጤት ማምጣታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

– ለደረጃውና ለእርከኑ የተመደበውን ትምህርት በትክክል ማጠናቀቃቸውን ፣ በት/ቤቱ መረጃ ወይም በብሔራዊ ፈተና ውጤት መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

13. በማረጋገጫ የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች

– ለየክፍሉ ትምህርት ማጠናቀቂያ ወይም የሴሚስተር ፈተና ውጤት መግለጫ ወይም የተማሪ ሪፖርት ካርድ በየዓመቱ ለተማሪ ይሰጣል፡፡
– ተማሪው የአንዱን እርከን ትምህርት ሳያጠናቅቅ በየእርከኑ መካከል ትምህርት ቤት ቢቀይር ከሚለቅበት ት/ቤት የሚሰጠው የየክፍሉ የተጠናቀረ ዝርዝር ው□□ /ትራንስክሪፕት/ እና የመልቀቂያ ሕጋዊ ሰርተፊኬት የተወሰኑ የትምህርት ደረጃ ማጠ ናቀቂያ መግለጫ ይሆናሉ፡፡

- በየርከኑ መጨረሻ ክፍል የሚሰጥ የትምህርት ውጤት ሕጋዊ መግለጫ / ትራንስክሪፕት/ እና የብሔራዊ ወይም አገራዊ ፈተና የሚሰጥበት ደረጃም ከሆነ የብሔራዊ ወይም የአገራዊ ፈተና ውጤት ሕጋዊ መግለጫ ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ መብቃታቸውን ማረጋገጫ ይሆናል፡፡
- በየርከኑ መጨረሻ የሚሰጥ የትምህርት ማስረጃዎች ወይም ሰርተፊኬቶች በማስተማሪያ ቋንቋ ወይም በአገር አቀፋዊ የሥራ ቋንቋ ወይም በክልላዊ የሥራ ቋንቋ ተዘጋጅተው ይሰጣሉ ፡፡

14. የት/ቤት፣የአካባቢው ማኅበረሰብ/ ኮሚኒቲ/ **እና የወላጅ** ግንኙነት

- አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲቋቋም የአካባቢው ህብረተሰብ የሚፈልገውን ጥቅም እንዲሰጥ ሆኖ ይደራጃል፡፡ ማኅበረሰቡም የትምህርት ቤቱን መቋቋም ጥቅም ተገንዝቦ የመማር ማስተማሩን ሥራ በተገቢው መንገድ እንዲተገበር ቀጥታ ግንኙነት ያደርጋል፡፡ የመማር ማስተማር ሥራ የትምህርት ቤቱንና የአካባቢውን ህብረተሰብ አባላት በትምህርት ቤቱ የለት ተዕለት ዕንቅስቃሴ ዙሪያ ተሣትፎአቸውን በሚከተሉት መድረኮች ሊገልጹ ይችላሉ።
    - የትምህርትና ሥልጠና አመራር፣
        1) በትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ
        2) በወላጅ መምህር ህብረት /ወመህ/

  የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ ይመራል። ይህ ቦርድ ከህብረተሰቡ፣ ከት/ቤቱ ማህበረሰብና ከቀበሌ መስተዳድር የተውጣጡ አባላት ሲኖሩት በመልካም ሥነምግባራቸውና በአመራር ችሎታቸው የተመሰገኑ ሆነው የቦርድ ሰብሳቢ ከቀበሌ መስተዳድር የሚወከል ሲሆን የት/ቤቱ ርዕሰ-መምህር የቦርድ ፀሐፊ ይሆናል።

  ✓ **የትምህርት ቤቱ፣ የአካባቢው ማህበረሰብና የወላጅ ግንኙነት ዓላማ፣**

    - ት/ቤቱ በትምህርት ዘመኑ ያከናወናቸው ተግባራትና ያጋጠሙት ችግሮችን ለህብረተሰቡ ለማሳወቅና መፍትሄ ለመሻት፣
    - ኅብረተሰቡ የትምህርት ቤቱን ችግርና ዕቅድ ተረድቶ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንዲችል፡፡

- ስለተማሪዎች የትምህርት ውጤት ወላጆች አውቀው ተገቢውን ክትትል በማድረግ ድጋፍ እንዲያደርጉ፤
- የወላጆችንና የመምህራንን ግንኙነት ለማጠናከርና የትምህርቱ ውጤት ይበልጥ የተሻለ እንዲሆን ለማስቻል፤
- .ትምህርት ቤቱን ለማጠናከር በሚቀርብ ዕቅድ ላይ ውይይት በማካሄድ ፤ መርምሮና አሻሽሎ በማጽደቅ አፈጻጸሙን ለመከታተልና ለመቆጣጠር፣
- ሥርዓተ ትምህርቱ ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ተጣጥሞና ተዛምዶ ለተማሪዎቹ መቅረቡንና ችግር ፈቺ መሆኑን ለመከታተልና □□□ ለመስጠት

✓ **የትምህርት ቤቱ አመራር** ድርሻ፣

- ➢ የተማሪዎችን ወላጆች ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ በመጥራት በልዩ ልዩ የትምህርት ጉዳዮች ላይ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት፡፡
- ➢ በአካባቢው የልማት ሥራ በመሳተፍና የተለያዩ ክበባትን አቋቁሞ ትምህርታዊና አዝናኝ የሆኑ ፕሮግራሞች በማዘጋጀት ለአካባቢው ህብረተሰብ አስተዋጽ ያደረጋል፣
- ➢ በአካባቢው ማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ማለትም የኢኮኖሚ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍና አዳዲስ ሀሳቦችን በማመንጨት የመፍትሄ ሀሳቦች የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡
- ➢ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል፣ ውጤትና ሥነምግባር በሚመለከት ጉዳዮችን በየጊዜው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
- ➢ ተማሪዎች ለመማር ተግባር የሚያስፈልጋቸውን የትምህርት ቁሳቁሶች እንዲያሟሉላቸው በማሳወቅ ተግባራዊነቱም ይከታተላል፡፡

**የተማሪ ወላጅ ድርሻ፣**

- ➢ ት/ቤቶች በሚያዘጋጁቸው የምክክር መድረኮች ላይ በመሳተፍ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ይወጣሉ፡፡
- ➢ የልጆቻቸውን የትምህርት አቀባበልና የሥነምግባር ሁኔታ በየጊዜው በመከታተል ለት/ቤቶች ግብረ መልስ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡
- ➢ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እንዲሁም በጉልበት ት/ቤቱን ማገዝ ይጠበቅባችዋል፡፡

- የአካባቢውን ህብረተሰብ ለትምህርት ቤቱ የልማት እንቅስቃሴ የማስተባበር ሃላፊነት አለባቸው::

**የአካባቢው ህብረተሰብ ድርሻ፣**

- ትምህርት ቤቱ፣ለተማሪዎችና ለት/ቤቱ ሠራተኞች ደህንነት ሲባል የሚያደርጋቸው እንስቃሴዎች ላይ በጋራም ሆነ በተናጠል በመሳተፍ አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
- ት/ቤቱ የራሱ ሀብት እንደሆነ ተገንዝቦ መንከባከብና መጠበቅ አለበት፡፡